የሰ/መ/ቁ 42309

ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን - ሳሙኤል ተገኑ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የመድን ዋስትና ውልን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ለአመልካች መኪና የመድን ዋስትና ሰጥቶአል፡፡ መኪናው ሲሽከረከር በነበረ ጊዜ በመገልበጡ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ተጠሪም የገባውን የመድን ዋስትና ግዴታ መሠረት በማድረግ ገንዘቡን ወጪ አድርጎ መኪናው የተገለበጠው በሹፌሩ ሳይሆን በብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠት አቁሞ በነበረበት ጊዜ የተበላሸውን ፍሬን እያስተካከለ የነበረው መካኒክ ሥራውን ሲሞክር መሆኑን ስለደረስኩበት ኃላፊነት ሳይኖርብኝ ለጥገና ያወጣሁት ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት በአመልካች ላይ ክስ መስርቷል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ክሱ በንግድ ሕግ ቁ 674(1) ወይም (2) መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦአል፡፡ የስረ-ነገር ክርክር በማንሳትም ተከላክሎአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከመረመረ በኋላ የተጠሪን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ በመቀበል ክስ የቀረበበትና ገንዘብ ከነወለዱ እና የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፈለው ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ታሕሣሥ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጸመ ያለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም የአመልካችን የይርጋ ክርክር የታለፈው በአግባቡ ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው የክርክር ጭብጭ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ወይስ አልሆነም? የሚለው ነው፡፡ ይህ ጭብጥ ግራቀኝ ወገኖችን ያከራከረ ወይም ግራቀኝ ወገኖች የተለያዩት የሕግ አግባብ /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.246(1)/ በመሆኑ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር ተገናዝቦ የሚታይ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ግን ወደሕጉ ከመኬዱ በፊት ከዚህ የተያያዘው የፍሬ ነገር አግባብ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

በግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንደተመለከተው ተጠሪ ክሱን ያቀረበው ሚያዝያ 3 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሆን ለክሱ መነሻ የሆነው ጉዳት ደረሰ የተባለው ደግሞ ግንቦት 12 ቀን 1994 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ጊዜ ማለትም ጉዳቱ በደረሰበት እና ክሱ በቀረበበት መሃል ያለው ሲታሰብ አራት ዓመት ከአስር ወር በላይ ነው፡፡ ይህ እንግዲህ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ ሲሆን፣ እውነታው ከየትኛው ሕግ ጋር ሲገናዘብ ነው ለይርጋው ክርክር አወሳሰን አግባብነት የሚኖረው የሚለውን ደግሞ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪ ገንዘቡ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት ወደክስ ሊያመራ የቻለው የመድን ሽፋን ባልሰጠሁበት ሁኔታ የወጣ ነው የሚል ምክንያት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች ሁለት የፍሬ ነገር አግባቦችን በመጠቀስ ክሱ በንግድ ሕግ ቁ 674 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ተከራክሮአል፡፡ የፍሬ ነገር አግባቦቹም የመጀመሪያው አደጋው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ተጠሪ የአደጋውን መንስኤ ካወቀበት ግንቦት 26 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ ክሱ እስከ ቀረበበት ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ክሱ በንግድ ሕግ ቁ 674(1) ወይም (2) መሠረት በይርጋ ቀሪ ነው ሊባል ይገባል ብሎአል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ክርክር የተጠቀሱት የፍሬ ነገር አግባቦች ትክክል አይደሉም የሚል ክርክር የለውም፡፡ የሚከራከረው ያቀረብኩት ክስ ያለአግባብ የተከፈለን ገንዘብ እንዲመለስ የሚጠይቅ በመሆኑ ተጠሪ በጠቀሰው ሕግ መሠረት በይርጋ ቀሪ አይሆንም፡፡ ሕጉ ለተያዘው ክርክር አግባብነት የለውም በማለት ነው፡፡

ተደጋግሞ እንደተገለጸው የግራቀኝ ወገኖች ግንኙት መነሻው የመድን ዋስትና /የኢንሹራንስ/ ውል ነው፡፡ ተጠሪ መኪናውን ያስጠገነው የውል ግዴታ እንዳለበት በማመን ነው፡፡ በኋላ ግን የጉዳቱን አደራረስ ወይም ሁኔታ ባውቅ ኖሮ መኪናውን አላስጠግንም ነበር፡፡ ጉዳቱ የደረሰው በመድን ዋስትና ውሉ ባልተሸፈነ ሁኔታ ነው የሚል ምክንያት አንስቶአል፡፡ ይህ አይነቱ የተጠሪ ክርክር ከተገባው ውል ውጪ በተሸሸገ ምክንያት ወይም በሐሰት በቀረበ ጥያቄ መሠረት እኔም ልሳሳት ችያለሁ ከሚል ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ በተሸሸገ ወይም በሐሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ ያጋጠመ ሲሆን፣ የይርጋው ዘመን የሚታሰበው ኢንሹራንስ ሰጪው የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁ. 674(2) ተደንግጎአል፡፡ የይርጋው ዘመን ሁለት ዓመት እንደሆነም በዚሁ ቁጥር ንኡስ ቁ (1) ተመልክቶአል፡፡ተጠሪ ክሱን ያቀረበው የተደበቀ ነገር መኖሩን ካወቀ ከሁለት ዓመት በላይ ቆይቶ እንደሆነም በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ በመሆኑም አመልካች የንግድ ሕጉን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መከራከሩ ተገቢ ሲሆን የተጠሪ ክርክር ግን የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ሲጠቃለል ተጠሪ ክሱን ያቀረበው በሕጉ በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ በመሆኑ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.86581 ታሕሣሥ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63225 ህዳር 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ በይርጋ ቀሪ በመሆኑ አመልካች ገንዘቡን እንዲመልስ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

# ውክልና